10ኛ ዓመት ቁጥር 59
10th Year No. 59

ባህር ዳር ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ/ም
Bahir Dar 27 July, 2005

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 32.05
Unit price -----

ማውጫ	Content
አዋጅ ቁጥር 118/1997 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርና ምርምር ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ	Proclamation No. 118/2005 The Amhara National Regional State Agricultural Research Institute Establishment Proclamation Amendment Proclamation.

አዋጅ ቁጥር 118/1997 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ምርምር ተቋምን ማቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በሀገሪቱ የገጠር ልማት ፖሊሲ መሠረት የክልላችን የግብርና ምርምር ሊያተኩርባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በግልፅ መለየትና ተልዕኮውን መወሰን በማስፈለጉ፣

ተቋሙ በተደራጀበት አዋጅ መሠረት ልማቱን የሚደግፍ ቴክኖሎጂዎችን ከማፈላለግና ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ከማላመድ አልፎ በቴክኖሎጂ ብዜት ላይ ጭምር እንዲሰማራ የተፈቀደለት አሠራር የምርምሩን የትኩረት አቅጣጫ እንደሚያዛባ ስለታመነበትና ይኸው ኃላፊነት በሌላ ህግ ለክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የተሰጠ በመሆኑ፤

Proclamation No. 118/2005

A Proclamation Issued to Amend the Amhara National Regional State Agricultural Research Institute Establishment Proclamation

WHEREAS, it is necessary to clearly identify concerns which the Agricultural research of our Region has to focus and define its mission thereto on the bases of rural development Policy of the Country;

WHEREAS, the working procedure which is allowed for the Institute, pursuant to its organizational establishment Proclamation, to additionally involve in the multiplication of technologies beyond from the search for technologies assisting development activities and adapting same to the objective reality of the Region has thus been believed to pervert the focus of the agricultural research direction and such responsibility has, however, been entrusted to the Regional Agricultural and Rural Development Bureau by virtue of other law;

የተቋሙን ዓላማ አግባብ ባላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አድርጐ እንደገና መቅረፅና የማስፈፀሚያ አደረጃጀቱንም ለተልዕኮው መሣካት በሚበጅ አግባብ ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it is found appropriate to re-design the objective of the Institute on the basis of relevant policies and strategies and to amend its organizational structure of execution in conformable with the attainment of its mission;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional State, in accordance with the Provision of Article 49 sub-art 3/1/ of the Revised Constitution of the Regional State, hereby issues this Proclamation.

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርና ምርምር ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 118/1997 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ::

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Agricultural Research Institute Establishment Proclamation Amendment Proclamation No. 118/2005."

2. ማሻሻያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርና ምርምር ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 48/1992 ዓ.ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

2. Amendments

The Amhara National Regional State Agricultural Research Institute Establishment Proclamation No. 48/2000 is hereby amended as follows:

ሀ. የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዞ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል::

A. Sub-Article 3 of Article 2 of the proclamation is hereby deleted and replaced with new sub Article 3 here below.

3. "የግብርና ምርምር ማዕከላት " ማለት ተቋሙ ተግባሩን ለመፈፀም ይቻለው ዘንድ አጥንቶ ለቢሮው የሚያቀርባቸውና በክልሉ መንግስት ዕውቅና የተደራጁና ወደፊት የሚደራጁ የምርምር ማዕከላት ናቸው ::

3. "Agriculture Research Centers" means research centers which the Institute studies and presents to the Bureau and thereby to have been and to be established under the recognition of the Regional Government with a view to enabling the Institute execute its duties.

ለ በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር ከንዑስ አንቀጽ 5 ቀጥሎ ከዚህ በታች የተመለከቱት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 ታክለዋል ::

B. The following new sub-Articles 6 and 7 are hereby added next to sub-Article 5 under Article 2 in the Proclamation.

6. " ቢሮ " ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ነው::

6. " Bureau" means the Amahra National Regional State Agriculture and Rural Development Bureau.

7. «የግብርና ቴክኖሎጂ» ማለት የግብርና ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ማናቸውም መሣሪያች፣ የዕፅዋት፣ የእንስሣትና የደን ዛፍ ዝርያዎች፣ የተሻሻሉ የግብርና አሰራሮች፣ ዘይቤዎችና የመሣሰሉትን ያጠቃልላል::

7. " Agricultural Technology" includes any implements, species of plants, animals and forest trees, improved agricultural practices, systems and the like which are helpful to speed up agriculture development.

ሐ. የአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል::

C. Sub-Article 2 of Article 3 of the Proclamation is hereby deleted and replaced with the following new sub-Article 2:

2. የተቋሙ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ለቢሮው ይሆናል ::

2. The Institute shall be accountable to the Head of the Regional Government and to the Bureau.

መ. የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

D. The Provision of Article 4 sub-Article 1 is hereby amended as follows:

1. የመንግስትን የልማት ፖሊሲዎች በማስፈፀም የክልሉን ህዝብ ኑሮ ለማሻሻል ይቻል ዘንድ ለግብርና ልማት መፋጠን ማነቆ የሆኑ ችግሮችን መለየትና እነዚህንም ለማቃለል በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ተግባር ላይ ውለው ውጤት ያስገኙ መፍትሄዎችን በማምጣትና ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማላመድ የመነሻ ቴክኖሎጂዎችን ወይም ናሙናዎችን ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጩ ማዘጋጀት ::

1. Identify and alleviate problems that are impediment for the expedition of agricultural development and thereby introduce solutions which have been practically in use at home as well as abroad and adapt them to the objective realities of the Region, and cause initial technologies or samples to be disseminated to end users in order to improve the living of the people of the Region by implementing development policies of the government;

ሠ. የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች እንደሚከተለው ተሻሽለዋል::

E. Provisions of sub-Articles 1 and 2 of Article 5 of the proclamation are hereby amended as follows: -

1. የግብርና ምርምር አማካሪ ቦርድ ከዚህ በኋላ «ቦርድ» እየተባለ የሚጠራ፤

1. Agricultural Research Advisory board herein after referred to as "Board".

2. በቢሮው አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተርና ዳይሬክተሮች።

2. A Director General, a Deputy Director and Directors to be appointed by the Head of the Regional Government upon the recommendation by the Bureau.

ረ. የአዋጁ አንቀጽ 6 ተሰርዞ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ አንቀጽ 6 ተተክቷል ::

F. Article 6 of the Proclamation is hereby deleted and replaced with the new Article 6 here below.

6. ስለቦርዱ አባላት

ቦርዱ ሰብሣቢውን ጨምሮ በቢሮ ሀላፊው የሚሰየሙ ከ5 እስከ 7 አባላት ይኖሩታል።

6. Members of the Board

The Board shall have a chairperson and 5 to 7 members to be appointed by the Head of the Bureau.

ሰ. የአዋጁ አንቀጽ 7 ሙሉ በሙሉ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 7 ተተክቷል።

G. Article 7 of the proclamation is hereby wholly deleted and replaced by new Article 7 here below.

7. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ተቋሙ የሚያካሂደው ምርምር በመንግስት የፖሊሲ ፍላጐት ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ ይገመግማል ፣ አዳዲስ ጠቃሚ የምርምር ሃሣቦችን ለማመንጨት የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፣ ምርምር እንዲካሄድባቸው በየጊዜው አቅጣጫ ይሰጣል ፣

2. የተቋሙን ዓላማ ለማሣካት በሚረዱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ያማክራል፣ ሃሣብ ያቀርባል፣

3. የራሱን የውስጥ ደንብ አዘጋጅቶ ቢቢሮው ሲፀድቅለት ተግባራዊ ያደርጋል።

7. Powers and Duties of the Board

The Board shall, being accountable to the Bureau, have the powers and duties here below:

1. Evaluate that the research undertaken by the Institute is based on the policy requirements if the government, formulate mechanisms enabling to generate new important ideas of research and give directions all the time to conduct a research on same thereof;

2. Advise on other issues which are helpful to attain the objective of the Institute, and give suggestions thereto;

3. Prepare and thereby implement its own internal rules and regulations upon approval by the Bureau.

ሸ. የአዋጁ አንቀጽ 9 ተሰርዞ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

H. Article 9 of the Proclamation is hereby deleted and amended as follows:

9. የተቋሙ ስልጣንና ተግባር

ተቋሙ ቀጥሎ የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአገሪቱ የሣይንስና ቴክኖሎጂ፣ የግብርና ልማትና ምርመር ፖሊሲዎች መሠረት የክልሉን የግብርና ምርምር ማስተር ፕላን ተግባራዊ ለማድረግ የምርምር ቅደም ተከተል መወሰን፣ የስራ ፕሮግራምና እቅድ ማውጣት፣ በክልሉ መንግስት ሲፀድቅም ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም በሚመለከታቸው ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፤

2. የክልሉን የግብርና ምርምር ፖሊሲ መንደፍ፣ የማሻሻያ የፖሊሲ ሃሣብ በማመንጨት ማቅረብና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

3. በግብርና ላይ ተሰማርቶ የሚገኘውን ህብረተሰብ በተነፃፃሪ አጭር ጊዜ ውስጥ ከድህነት ለማውጣትና ወደ ላቀ የኢኮኖሚ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችሉ ፣ የተለያዩ የስነ-ምህዳር ቀጠናዎችን መሠረት ያደረጉና በማላመድ ላይ የተመሰረተ አግባብን በጥብቅ በመከተል የሚቀረፁ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ማዘጋጀት፤

4. ከክልሉ የልማት ፍላጐት ጋር የሚጣጣሙ የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ለመቅረፅና ለማዘጋጀት የሚያስችል መመሪያ ማውጣት፣ በአግባቡ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በጀት መገምገምና በመመሪያው መሠረት መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፤

5. በክልሉ የግብርና ምርምር ፖሊሲና ስትራቴጅ መሠረት የግብርና ምርምር ማከናወን ወይም እንዲከናወን ማድረግ፤

9. Powers and Duties of the Institute

The Institute shall have the powers and duties here below:

1. Determine research priorities to effect the Regional Agricultural Research Master Plan that has been formulated based on the country's science and technology and policies of agricultural development as well as research; develop work plans and programs and implement them when approved by the Regional Government; follow up the execution of same thereof;

2. Formulate the Regional Agricultural Research Policy, initiate updated policy proposals and submit it to the Board and implement same upon approval;

3. Prepare perpetually agricultural technologies formulated based on different agro-ecological zones and pursuing strictly the relevancy to adaptation in order to enable the community taking part in agricultural activities extricate from poverty and transform itself to the highest economic status in a relatively short period of time.

4. Issue guidelines for the proper formulation and preparation of agricultural research programs and projects in line with the Region's development requirements; and thereby evaluate whether the proposed projects, programs and budget are prepared in accordance with the guidelines;

5. Undertake or cause the undertaking of agricultural research activities on the bases of the Region's Agricultural Research policy and strategy;

6. በክልሉ ውስጥ የተለያዩ የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚቋቋሙበትንና የሚደራጁበትን ሁኔታ በየጊዜው እያጠና ለቢሮው ማቅረብና ሲፈቀድም በተግባር ላይ ማዋል፤ በክልሉ የግብርና ምርምር ማስተር ፕላን ላይ በመመርኮዝ ማንኛውንም በተቋሙ ስር የሚተዳደር የግብርና ምርምር ማዕከል አደረጃጀት በየጊዜው መገምገም በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ወይም እንዲታጠፍ ለቢሮው ሃሣብ ማቅረብና ሲወሰንም ተግባራዊ ማድረግ ፤

6. Study regularly and submit to the Bureau conditions in which various agricultural research centers are established and organized in the Region and implement same up on approval; evaluate frequently the organizational structure of any research center under the Institute and propose to the Bureau to newly establish or dissolve same on the bases of the Regional Agricultural Research Master Plan and implement it upon approval thereof;

7. የግብርና ተመራማሪዎችን ለበለጠ ውጤት የሚያነሣሱ አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ አርሶ አደሮች ዘንድ ደርሰው ባስገኙት ተጨባጭ ለውጥ ላይ በዋናነት የሚመሠረቱ የዕድገት መሠላሎችን ማዘጋጀትና ሲፈቀድም በተግባር ላይ ማዋል ፤

7. Create conducive conditions which initiate agriculture researchers for greater results, prepare career structures for researchers depending mainly on real changes which they bring about by outreaching farmers and implement same upon approval thereof;

8. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስ ለማስፋት በምርምር የተገኙ ውጤቶችን ማስተዋወቅ፣ አመቺ የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ተገቢውን ተግባር ማከናወን፤

8. Advertise, in collaboration with appropriate organs, agricultural research results in order to broaden the society's agricultural scope of knowledge, and undertake appropriate task using suitable mass media,

9. በክልሉ፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተካሄዱና በሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችና የምርምር ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ ማከማቸትና ማሰራጨት፣የመረጃ ቅብብሎሽ ስርአትን መገንባትና መምራት፤

9. Collect, organize and disseminate information on agricultural research activities and results that have been and to be carried out in the Region, else where in the country and the world; develop and coordinate information exchange mechanisms thereto,

10. በክልሉ ግብርና ምርምር ላይ የሚሰማራ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራትና ያለውንም ለማሻሻል በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ተሣትፎ ማድረግ፣ በተቋሙ የተሰማራውንም የሰው ኃይል አቅም ማሣደግና መገንባት የሚያስችል ስልት መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፤

10. Participate in efforts exerted for the development and upgrading of human resources working on the Regional agricultural research; formulate and implement a strategy enabling to develop and build up the capacity of human resources involve in the Institute.

11. በክልሉ ግብርና ምርምር የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ሰዎች ወይም ተቋሞች ሽልማት የሚሰጥበትን ስርዓት መዘርጋት፣ሽልማት ወይም ማበረታቻ መስጠት፤

12. በግብርና ምርምር መስክ የተቋቋሙትን ወይም የሚቋቋሙትን የሙያተኞች ማህበራት ማበረታታት እንዲሁም ለግብርናው ምርምር በመረጃዎች ልውውጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

13. አግባብ ባለው ህግ መሠረት በሃገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግብርና ምርምርና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ጠቃሚ ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ ሌሎች አካላት ጋር ግንኙነቶችን መመስረትና በቢሮው ዕውቅና የትብብር ስምምነቶችን መፈራረም፤

14. የክልሉን ግብርና ምርምር በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ መሣተፍና የክልሉን መንግስት ማማከር፤

15. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉና በፌዴራሉ የግብርና ምርምር ማዕከላት አማካኝነት በሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ ያልሆኑ የስራ ድግግሞሽና የሃብት መባከን እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት፤

16. በክልሉ ውስጥ በግብርና ምርምር ስራ ላይ የተሰማራን ወይም የሚሰማራን ማንኛውንም ሰው መዝግቦ ዝርዝሩን መያዝ፣ ስታንዳርድ በማውጣት ስራውን መከታተልና የምርምር ጥራቱን መቆጣጠር፤

17. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ መክሰስና መከሰስ፤

18. ለቢሮውና ለሚመለከታቸው አካላት በየወቅቱ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ፤

19. ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን::

11. Establish a system of award to persons or institutions which have a record of highest achievements in agricultural research activities of the Region; provide an award or incentive thereof;

12. Encourage professional associations which have been or to be established in the field of agricultural research, and create an enabling condition to facilitate their contribution for the agricultural research activity through information exchange;

13. Establish relations, pursuant to relevant law, with agricultural research and higher education institutions found at home and abroad as well as with other bodies which are able to provide useful assistances, and conclude agreements with same under the recognition of the Bureau;

14. Participate in all affairs concerned with agricultural research of the Region and consult the Regional Government thereon;

15. Establish, in cooperation with relevant bodies, a system of evaluation in order to avoid unnecessary duplication of efforts and wastage of resources on research projects conducted by the Regional and Federal Agricultural Research Centers;

16. Register and maintain the list of any person involved or to be involved in an agricultural research activity in the Region and follow up the activity and thereby control the quality of the research by setting a standard;

17. Own properties, enter into agreements, sue and be sued;

18. Submit periodically a performance report to the Bureau and concerned bodies;

19. Accomplish other related tasks necessary for the attainment of its objectives.

ቀ. የአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2፣3፣4፣5፣7 እና 8 ድንጋጌዎች ተሰርዘው ከዚህ በታች በተመለከቱት አዳዲስ ንዑሳን አንቀጾች ተተክተዋል።

2. የተቋሙንና የግብርና ምርምር ማዕከላቱን በጀት ያዘጋጃል፣ ለቢሮው ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል፤

3. አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተመራማሪዎችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

4. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ተቋሙን ይወክላል፤

5. የተቋሙን የስራ አፈፃጸምና የሂሣብ ሪፖርቶች አጠናቅሮ ለቢሮውና አግባብ ላላቸው ሌሎች አካላት በየወቅቱ ያቀርባል፤

7. በቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

8. ለተቋሙ ስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች የበታች የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

በ. የአዋጁ አንቀጽ 11 ተሰርዞ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ አንቀጽ ተተክቷል።

11 ነባር የምርምር ማዕከት ስለሚተዳደሩበት ሁኔታ፡-

1. ቀደም ሲል የተቋቋሙት የክልሉ ግብርና ምርምር ማዕከላት በተቋሙ ስር መተዳደራቸውን ይቀጥላሉ፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም እስካሁን ድረስ በተቋሙ ስር የነበሩት የቴክኖሎጂ ብዜት ማዕከላት ከተቋሙ ወጥተው በቢሮው ስር ይደራጃሉ፤

i. The provisions of sub-Articles 2,3,4,5,7 and 8 of Article 10 of the proclamation are hereby deleted and replaced by new sub-Articles here below:

2. Prepare and submit to the Bureau budget for the Institute and Agricultural Research center, and implement same upon approval;

3. Employ and administer researchers pursuant to relevant law;

4. Represent the Institute in all its relations with third parties

5. Consolidate performance and financial report of the Institute and periodically submit same to the Bureau and other relevant bodies;

7. Perform other functions given to it by the Bureau;

8. May delegate part of his powers and duties to other subordinate officials and staff to the extent required to expedite the activity of the Institute.

J. Article 11 of the proclamation is hereby deleted and replaced by new sub-Article here below:

11. Administration of former Research Centers

1. Formerly established agricultural research centers of the Region shall continue under the administration of the Institute.

2. Notwithstanding the provision of sub-Article 1 hereof, technology multiplication centers, which have been hitherto under the Institute, shall be withdrawn from the Institute and be organized under the Bureau.

3 የምርምርና የብዜት ስራዎችን አጣምረው ሲሰሩ የነበሩ ማዕከላት ስለሚተዳደሩበት አግባብ ቢሮው ዝርዝር መመሪያ ያወጣል::

ተ. የአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 5 ሙሉ በሙሉ የተሰረዘና ንዑስ አንቀጽ 6 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5 ሆኖ የተስተካከለ ሲሆን የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 4 ድንጋጌዎች በሚከተለው አኳኋን ተሻሽለዋል ::

1. የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ኖሯቸው በተቋሙ በኩል የሚሰጣቸውን ተልዕኮ መሠረት በማድረግ የመንግስትን ፖሊሲ የተከተሉ የግብርና ምርምር ተግባራትን ማከናወን፤

4. የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የስራ ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ለተቋሙ ማቅረብና ሲፈቀድላቸው በተግባር ላይ ማዋል::

ቸ. የአዋጁ አንቀጽ 13 ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ የተሰረዘ ሲሆን በዚሁ ምክንያት ከአንቀጽ 14 እስከ 18 ያሉት ድንጋጌዎች አንቀጽ 13፣14፣15፣16፣ እና 17 ሆነው ተስተካክለዋል::

3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

3. The Bureau shall issue a detailed directive relating to the administration of centers that have carried out research and multiplication activities in combination.

K. Sub Article 5 of Article 12 of the proclamation is hereby wholly deleted and the previous sub Article 6 is arranged being sub-Article 5, and the provisions of sub- Articles 1 and 4 of this Article are amended as follows:

1. Undertake agricultural research activities which are adherent to the policy of the government based on the mission given to them by the Institute having their internal administrative autonomy;

4. Prepare and submit to the Institute short and medium term work programs and implement same upon approval.

L. Article 13 of the proclamation is hereby wholly deleted; and accordingly, the provisions from Articles 14 to 18 are arranged being Articles 13,14,15,16 and 17 respectively.

3. Effective Date

This proclamation shall come into force as of its publication in the ***Zikre Hig Gazzeta*** of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 27th day of July 2005.

Yosef Retta
President of the Amhara National Regional State